# አንዱዓለም ስለ ኢሕአፓ ከሰጠው 9 አስተያየቶች በ7ቱ ተሳስቷል

ከመልካሙ በረከት

አንዱዓለም ተፈራ ትግላችንን እንመርምር በሚለው ጽሁፉ ትግሉን ሳይሆን ድርጅቶችን ሲመረምር በማየቴ ገርሞኛል፡፡ ርዕሱ ድርጅቶችን እንመርምር ቢለው ሳይሻል ይቀር? ያምሆነ ሌላ ስለ ኢሕአፓ የጻፈው መረቅ የሌለው ነው፡፡ በግምት ወይም እንደ አንዱዓለም በስማ በለው አይደለም የምጽፈው፡፡ የድርጅቱ አባል በመሆነ የማውቀውን ነው የምጽፈው፡፡ በርግጥ ጸሃፊው ሁለት ሃቆችን ተናግሯል፡፡

አንደኛው ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ከዳር እስከ ዳር በሕዝብ የተደገፈ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከአርባ ዓመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ ጠንካራ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጸሃይ የሞቀ ዕውነት ነው።

<u>ከጸሃፊው ጋር የማልስማማባቸው ሰባቱ ነጥቦቹ፡-</u>

1. መቼም ሶስት አባላት የያዘም ድርጅት ከተባለ "<u>እስከመቼም</u>" ድርጅት ሊባል ይችላል። ነገ ደግሞ <u>እስከመቼ ዴሞክራሲያዊ</u> የሚል ቢፈጠር መገረም የለብንም፡፡ **በመካከላቸው ያለው ልዩነት እንኩአን ለውጭው ኢትይዮጵያውያን ለርራሳቸው አባላት እንኩአን የውጭው ሰው አባላልቱ አባላት ግልጽ ሳይሆን**. . . እንዴት ተደርጎ አንዱዓለም? ልዩነታችንማ የሰማይና የምድር ያህል ይራራቃል፡፡ የአርባ አመት የትግል ልምድ ያለን እንዴት አድርገህ ልዩነት የማናውቅ አድርገህ እንደገመትከን ገርሞኛል፡፡ ልዩነታችንን ለማወቅ በርካታ ጽሁፎች ተጽፈዋልና አንብብ፡፡ ወይም አጠገብህ ካለ አንድ ኢሕአፓ ለመረዳት ሞክር፡፡ የተለያየነው በመርህ ደረጃ ነው ሁሉን ትቼ ባጭሩ፡፡

2. **ግማሽ እግራቸውን (አንድ እግራቸውን ለማለት መሰለኝ) በትላንት ትግላቸው ሌላውን ደግሞ በምኞታቸው ተክለው** . . . ምን ለማለት እንደተፈለገ አልገባኝም፡፡ ቀና አባባል ይሆን ወይም ሰንካላ ለመረዳት አልቻልኩም፡፡ ምናልባት በሌላ ጽሁፍ ካልሰለቸው ያብራራ ይሆናል፡፡ ነገና ተነገወዲያ መሰረታቸው ትናንት አይደለም እንዴ?

3. **የትግሬዎች ነጻ አውጭ ግንባር መንግስት በሰላምም ሆነ በትጥቅ ትፍልም መወገድ አለበት ብለው በፖለቲካ ምህዳዳሩ አሉ** የሚለው የሃቀኛው ኢሕአፓ ኣቅዋም እንጅ የእንጃው አይደለም፡፡ አንዱ ልዩነታችን ይሄ ነው፡፡ አታደባልቀን፡፡ የሰላሙንና የመሳሪ ትግሉን <u>ሁለገብ ትግል</u> ነው የምንለው፡፡

4. **እንደ ሰማያዊ ፓርቲው ግልጽ አውጥተው ሕዝብ እንዲያውቀው ባያደርጉም እንደ ግንቦት ሰባት የተሸፋፈነ አይደለም።** ምኑን ነው ለሕዝብ ኢሕአፓ ግልጽ ያላደረገው? ምን ከሕዝቡ የደበቀው ጉዳይ አለ ይህ ላለፉት አርባ ሶስት አመታት በሕዝብ ታቅፎ የሚታገለው ኢሕአፓ? ጸሃፊው ስለኢሕአፓ ብዙም ባለማወቁ ሕዝቡም የኢሕአፓ ዓላማ አያውቅም ሊል ወስኗል፡፡

5. **እንደሌሎቹ ሁሉ አብዛኞዎቹ መግለጫቸው የወጡትና ሕዝብ የሚያውቃቸው የገዥውን ቡድን በማውገዝና ወንጀሉን በመዘርዘር ላይ ያተኮሩ ናቸው።** እና ገዥውን ቡድን ማውገዝ የለብንም

ነው አባባሉ፡፡ ሕዝቡ የሚያውቀውን ማለትስ ምን ማለት ነው፡፡ ሃቅ ቢደገም ምን ይከፋል፡፡ ውሸትን አይደለም የደገሙት፡፡ ቃሉ ጠፋው መሰለኝ ሊለን የፈለገው ተግባራዊ አይደላችሁም ለማለት ነው፡፡ ሰማይ ላይ ተቀምጦ በአጉይ መነጽር ኢሕአፓ ምን አንደሰራ ወይም እንደሚሰራ ማየት እንዳልቻለ ተረድቼዋለሁ፡፡ ዕውነትን መናገር ስድብ አይደለም፡፡ ወያኔ መጥፎ ነው ማለት ስድብ አይደለም፡፡ ቢሰደብም ለወያኔ አይበዛበትም፡፡ ከመሳደብ በላይ ልናጠፋው አይደል ትግላችን?

6. **ለምን አመርቂ የሆነ ትብብር ከሌሎች የትግል ድርጅቶች ጋር ፈጥረው መሄድ እንዳልቻሉና በተለይም በመካከላቸው ስምምነት ፈጥረው ለምን ወደፊት እንደማይሄዱ ለኔ ግልጽ አይደለም፡፡** ኢድሃቅንና ሕብረትን ብቻ ማንሳቱ ኢሕአፓ ከበርካታ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራቱን ማስታወስ በቂ ይመስለኛል፡፡ ምናልባት አነዚህን ሕብረቶች አልሰማህም ለማለት ይከብደኛል። ድርጅቱ አሁንም የሕብረት ጥሪ አቅርቧል፡፡ መስፈርቶችም አስቀምጧል፡፡ ምናልባት አልሰማህ ይሆናል፡፡

7. **ከቅርብ ጊዜ ሁለቱን ለማቀራረብ የተደረገው ጥረት በአንደኛው ወገን ተቀባይነት እንዳላገኘ ተረድቻለሁ፡፡** አንጃው ለመታረቅ ፈቃደኛ ሆኖ ኢሕአፓ እምቢተኛ ሆነ ተብለህ ነው የተነገረህ፡፡ ለምን ወደ ኢሕአፓ ጽ/ቤት ደውለህ እስቲ አስረዱኝ ለማለት ለምን ከበደህ? የሌሎቹ ድርጅቶች መከፈል ሳያስገርምህ የኢሕአፓ ለምን? በነገርህ ላይ አንጃ ለኢሕአፓ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ አንጃነት የሚፈጠረው በመርህ ካለመግባባት ነው፡፡

ጸሃፊው ሲያጠቃልል ሕዝብ የሚያውቀውን አዲስ ያልሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ደግመው ደጋግመው ቢችሉም ሁሌ ይህንኑ አባባል ቢደግመው ይደገፋል እንጅ **ሁሉ ሰው የተናገረውን** ብለን ልናሾፍበት አይገባም፡፡ ጸሃፊው ስለ ኢሕአፓ ያለው ግንዛቤ የተሟላ አይደለም፡፡ ሃቁን በሚገባ ስትረዳ ይህ ድርጅት ያኮራሃል፡፡ ወይም ሬዲዮ ስርጭቱን አዳምጥ፣ ፕሮግራሙን አንብብ፣ በርካታ ጹፎቹን አገላብጥ፡፡ በርግጥ የ43 አመትን ታሪክ መመርመ ቀላል አይደለም፡፡ የሚቀለው ግን በትዕግስት ለጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ የሚሰጡ ስላሉ ደውልላቸው፡፡ኢሕአፓ በተሳሳተበት ሁሉ ስህተቱን ገምግሞ ሂስ አቅርቦ እርማት ወስዷል፡፡ አካፋን አካፋ ማለቱ ትክክል ሲሆን አካፋውን ዶማ ማለት ግን ስህተት ነው፡፡